# የሐዋርያው ዮሐንስ መልእክት — ሁለተኛ

1ሽማግሌው፤

በእውነት ለምወዳት እኔ ብቻ ሳልሆን
እውነትን የሚያውቁ ሁሉ ለሚወዷት ለተ
መረጠችው እመቤትና ለልጆቿ፤ 2በውስጣ
ችን ከሚኖርና ከእኛ ጋር ለዘላለም ከሚሆን
እውነት የተነሣ፣ 3ከእግዚአብሔር አብና የአብ
ልጅ ከሆነው ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፣ ምሕረ
ትና ሰላም በእውነትና በፍቅር ከእኛ ጋር
ይሆናል።

4ከልጆችሽ አንዳንዶቹ ከአብ በተሰጠን
ትእዛዝ መሠረት በእውነት ጸንተው እየሄዱ
በማግኘቴ እጅግ ደስ ብሎኛል። 5አሁንም
እመቤት ሆይ፤ ከመጀመሪያ የነበረችውን
እንጂ አዲስ ትእዛዝ አልጽፍልሽም፤ ይኸ
ውም እርስ በርሳችን እንዋደድ ዘንድ ነው።
6ይህም ፍቅር፤ በትእዛዙ መሠረት እንመላለስ
ዘንድ ነው። ትእዛዙም ከመጀመሪያ እንደ
ሰማችሁት በፍቅር እንድትኖሩ ነው።

7ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደ መጣ የማ
ያምኑ ብዙ አሳቾች ወደ ዓለም ወጥተዋል።
እንዲህ ያለ ማንኛውም ሰው አታላይና የክር
ስቶስ ተቃዋሚ ነው። 8እናንተም የደከ
ማችሁበትን ዋጋ እንዳታጡ፣ ነገር ግን ሙሉ
ሽልማት እንድትቀበሉ ለራሳችሁ ተጠንቀቀ
። 9በክርስቶስ ትምህርት የማይኖርና
ከትምህ ርቱ የሚወጣ ሁሉ አምላክ
የለውም፤ በክ ርስቶስ ትምህርት የሚኖር
ግን አብም ወልድም አለው። 10ማንም
ወደ እና ንተ ቢመጣ፣ ይህንንም
ትምህርት ባያመጣ በቤታችሁ አትቀበሉት፤
ሰላምም አትበሉት፤ 11የሚቀበለው ሰው፣
የክፉ ሥራው ተባባሪ ይሆናልና።

12የምጽፍላችሁ ብዙ ነገር ነበረኝ፤
ይሁን እንጂ በወረቀትና በቀለም እንዲ
ሆን አልፈልግም፤ ዳሩ ግን ደስታችን ፍጹም
ይሆን ዘንድ ወደ እናንተ መጥቼ ፊት ለፊት
ላነጋግራችሁ ተስፋ አደርጋለሁ።

13የተመረጠችው የእኅትሽ ልጆች ሰላ
ምታ ያቀርቡልሻል።

1፥1 ቍ3:13፤ ዮሐ 8፥32፤ሐሥ11፥30፤ ሮሜ16፥13፤1ጢሞ 2፥4፤1ጴጥ5፥13፤ 3ዮሐ1
1፥2 ዮሐ14፥17፤ 2ጴጥ1፥12፤1ዮሐ1፥8
1፥3 ሮሜ1፥7
1፥4 ዮሐ3፥4
1፥5 1ዮሐ2፥7
1፥6 ዮሐ14፥15፤ 1ዮሐ2፥5:7
1፥7 ዮሐ1፥14፤ 1ዮሐ2፥18:22፤ 4፥1:2:3
1፥8 ማቴ10፥42፤ማር 10፥29:30፤1ቆሮ3፥8፤ ዕብ10፥35:36፤ 11፥26
1፥9 ዮሐ8፥31፤ 1ዮሐ2፥23
1፥10 ሮሜ16፥17
1፥11 1ጢሞ5፥22
1፥12 ዮሐ3፥29፤ 3ዮሐ13:14
1፥13 ቍ1